# ትችታችን በምክንያት እና በኃላፊነት ስሜት ይሁን!

## ይድረስ ለዶ/ር ሲሳይ መንግስቴ

***መግቢያ***

ሰሞኑን ለውይይት መነሻ እንዲሆኑ ሁለት ሰነዶችን ለመገናኛ ብዙሀን ማሰራጨቴ ይታወቃል። እነዚህ ሰነዶች የውይይት መነሻ ሰነድ ስለሆኑ የተሰራጩት ተገቢ ግምገማና ትችት እንዲቀርብባቸውና የበለጠ መዳበር እና መሻሻል እንዲችሉ፣ ከዚያም የጋራ መግባባት የተፈጠረባቸው የጋራ ትግል ሰነዶች እንዲሆኑ ታስቦ የቀረቡ ናቸው። ስለዚህ በሰነዶቹ ላይ የሚካሄድ ግምገማና የሚቀርብ ትችት የሚፈለግ እና እንደ ድጋፍ የሚቆጠር ነው። ሆኖም ግን የሚቀርቡት ትችቶች ከሰነዶቹ ትክክለኛ ይዘት ጋር ባልተያያዘ፣ በተዛባ ሁኔታ፣ ያልተባለን ነገር እንደተባለ አድርጎ በማቅረብ፣ በሰነዶቹ ይዘት ላይ ከማተኮር ይልቅ በጸሐፊው ሰብዕና ላይ በማተኮር የሚቀርቡ ከሆነ ውጤታቸው ገንቢ እና ጠቃሚ አይሆንም።

አንዳንዶች ሰነዶቹን በተገቢው ሁኔታ መተቸት የጀመሩ ሲሆን፣ አንዳንዶች ደግሞ ኃላፊነት በጎደለው መንገድ በጭፍን ጥላሸት የመቀባት ተግባር ሲፈፅሙ እያታየ ነው። እንዲህ ዓይነቱ ቅንነት የጎደለው አካሔድ ከወዲሁ ካልተተቸ እና ካልታረመ በስተቀር በቀጣይ በስፋት ሊካሄዱ በታሰቡት የግምገማና የትችት ሂደቶች ላይ የራሱን ጉዳት ሊያስከትል ይችላል። ህብረተሰቡም የተዛባ አመለካከት እንዲይዝ የማድረግ ጉዳት ያስከትላል። ከዚህ ጋር በተያያዘ ዶ/ር ሲሳይ መንግሥቴ ትንታኔ በሚሰጡበት መገናኛ ብዙሀን ላይ ሰሞኑን በሁለት ክፍል ያቀረቡት ኃላፊነት የጎደለው ትችት የችግሩ ጥሩ ማሳያ ሆኖ አግኝቸዋለሁ። በዚህም ምክንያት እሳቸው ባቀረቡት ትችት ላይ በእኔ በኩል በጽሑፍ የላኩላቸውን የሚከተለውን ቅሬታዬን የተወሰኑ ማሻሻያ በማድረግ በይፋ ለአንባብያን ማጋራት ተገቢ ሆኖ አግኝቸዋለሁ። ይህንን ማድረግ ያስፈለገው ቀጣዮቹ ግምገማዎች እና ትችቶች ተመሳሳይ ችግር እንዳይታይባቸው እና የተሻለ ውጤታማ እንዲሆኑ በማሰብ ነው።

ጤና ይስጥልኝ ዶ/ር ሲሳይ መንግሥቴ፣

በትናንትናው ዕለት በላኩልዎት ሰነድ ላይ ያቀረቡትን ክፍል አንድ ትችት አዳመጥኩት። ከልብ ነው የማመሰግነው። በትችትዎት ላይ ከአቋም ልዩነት፣ ከተዛባ ግንዛቤ፣ ሰነዱን በደንብ ካለማንበብ እና ካልተገባ የውይይት አቀራረብ የመነጩ በርካታ ህጸጾችን አይቻለሁ። እርስዎ የብልፅግና ፓርቲ ተዎካይ፣ እኔ ደግሞ የአገዛዙ ተቃዋሚ ስለሆንኩ በመካከላችን የአቋም ልዩነቶች መኖራቸው የሚጠበቅ ነው። የአቋም ልዩነቶች መኖራቸው በጎ እና ተፈጥሯዊ ስለሆነ በዚያ ረገድ በተንፀባረቁት ጉዳዮች ላይ እዚህ ላይ አስተያየት አልሰጥም። ነገር ግን ለቀጣይ ውይይቶች ጥራት ይረዳ ዘንድ ሰነዱን በአግባቡ ካለማንበብ፣ በአረዳድ ስህተት ወይም የተሳሳተ የአተቻቸት ስልት ከመጠቀም የመነጩ አንዳንድ ነጥቦችን ማንሳቱ ጠቃሚ ይሆናል ብዬ ስላሰብኩ እንደሚከተለው አቅርቤአቸዋለሁ።

1. **ትችት ሲያቀርቡ- “ሽግግሩን እውን ለማድረግ የ70 በመቶው ድርሻ የማን እንደሆነ ከአቶ ልደቱ ምንም የተነገረን ነገር የለም” ተብሎ የቀረበው ስህተት ነው።** የመጀመሪያው ገፅ፣ አንቀፅ 1፣ “የሰንጠረዡ ማብራሪያ” የሚለው ገፅ ላይ በግልፅ ተቀምጧል። እንዲህ ይነበባል- “… ቀሪው 70 በመቶ ለሽግግር ያለመብቃትና ከህልውና ጥፋት መትረፍ

*ያለመቻል እድላችን ግምት ነው” ይላል። ስለዚህ በቀረበው ግምት ላይ አልስማማም ብለው መተቸት ሲችሉ እርስዎ ግን የተፃፈን እንዳልተፃፈ አድርገው ማቅረብዎ ስህተት ነው።*

2. ***በመቶኛ የተጠቀሱት ቁጥሮች “የዕድል ግምቶች” ተብለው የቀረቡ እንጅ በመረጃ የተረጋገጡ እውነታዎች/Facts/ ናቸው ተብለው የቀረቡ እንዳልሆነ በሰነዱ ላይ በሚገባ ተገልጿል።*** *እርስዎ በእነዚህ ግምቶች አልስማማም ማለት ሲችሉ “የፖለቲካ ግምት በመቶኛ መቀመጥ የለበትም” ብለው ትችት ማቅረብዎ ስህተት ነው። በፖለቲካ ግምገማ የይሆናል ግምት ማቅረብ በሰፊው የተለመደ እና እርስዎም ሲያደርጉት የኖሩት አሰራር ነው።*

3. ***“በሰነዱ ላይ ሲቪክ ማህበራት እንዴትና በማን ሊመረጡ እንደሚችሉ የተጠቀሰ ነገር የለም” በማለት ያቀረቡት ትችትም ስህተት ነው።*** *ነፃ ሁኔታ ሲፈጠር በርካታ የውክልና ጥያቄ ሊቀርብ ስለሚችል የመመዘኛ መስፈርት መኖር እንዳለበት እና ይህንን ተግባር የማከናወኑ ስልጣንም የአገራዊ የውይይትና ድርድር ሒደት (አውድሂ) አስፈፃሚ ኮሚሽኑ እንደሆነ ገፅ 14፣ አንቀፅ 3 ላይ ተገልጿል። የተፃፈን እንዳልተፃፈ አድርገው ማቅረብዎ ስህተት ነው።*

4. ***“መረጃና ማስረጃ አላቀረበም” በማለት ያቀረቧቸው ተደጋጋሚ ትችቶች ተገቢ አይመስሉኝም።*** *የቀረበው ሰነድ በረቂቅ ደረጃ የቀረበ የእኔ እይታ ነው። አንድ ፖለቲከኛ እይታውን፣ አቋሙን ወይም የይሆናል ግምቱን ሲያቀርብ እንደ ፍርድ ቤት ክርክር፣ የምርምር ስራ ወይም የመመረቂያ ሰነድ ጥሬ ዳታ /Date/ ወይም መረጃ እና ማስረጃ ማቅረብ አለብህ አይባልም። የሶሻል ሳይንስ ጉዳይ ብዙውን ጊዜ አንፃራዊ /Subjective/ ነው። እርስዎን ጨምሮ ሁላችንም በየመገናኛ ብዙሀኑ በትንታኔ የምናቀርበው ሐሳብ በአብዛኛው የዕይታ፣ የግንዛቤ ወይም የአቋም ጉዳይ ነው እንጅ የምርምር ውጤት አይደለም። የኔ አይነት የፖለቲካ ሰው አንድን መንግሥት “አብዛኛው ህዝብ ይደግፈዋል ወይም አይደግፈውም” ብሎ ለመናገር የግድ ዳታ መሰብሰብ ወይም መጀመሪያ ህዝበ-ውሳኔ ማካሄድ የሚጠበቅበት አይመስለኝም። እኔም ሆንኩ እርስዎ የኢህአዴግን መንግሥት “አብዛኛው ህዝብ አይደግፈውም” እያልን ስንቃወመው የነበረው የተለየ ጥናት ስለሰራን አልነበረም። ይልቁንም አንዳንድ ፖለቲካዊ ጉዳዮች ከክርክር ባለፈ መጠን ግልፅ የሆኑ እውነታዎች ስለሆኑ ነው። ለብልፅግና ፓርቲ ሲሆን የተለየ መመዘኛ መጠየቅ ተገቢ አይመስለኝም። በአጭሩ፣ ስለ አገሪቱ ፖለቲካ በጥናት አድራጊዎች እየተፈለገ የሚጠየቅን እና ራሱ የመረጃ ምንጭ ለመሆን የበቃን የዕድሜ ልክ ፖለቲከኛ ስለ ፖለቲካ አቋምህ መረጃ እና ማስረጃ አቅርብ እያሉ መነዝነዝ ከአስተውሎት የመነጨ ተገቢ ትችት አይደለም።*

5. ***“መንግሥት እንዳለ የሚቆጠር አይደለም” ማለቴንም “እንደዚህ መባል የለበትም” ብለው ተችተዋል።*** *የወቅቱ መንግሥት በዚህ መጠን ሊገለፅ አይገባውም ብለው መከራከር ሲችሉ “መንግሥትን እንደዚህ ብሎ መተቸት አይቻልም” ብለው ትችት ማቅረብዎም ስህተት ነው። አንድን መንግሥት ከተግባሩ ተነስቶ፣ በተለይም ሰላምን እና የሕግ የበላይነትን ማስፈን ያቃተው ሆኖ ሲገኝ “እንዳለ የሚቆጠር አይደለም” ብሎ መተቸት መብት ከመሆኑም በተጨማሪ ችግር ያለው አገላለፅ አይመስለኝም። እንኳንስ እኔ የራሱ የመንግሥት አካል የሆነው ኢሰመኮም “መንግሥት ያለ አይመስልም” በማለት በአንድ ሪፖርቱ ላይ ገልፆታል። እንዲህ አይነቱ አገላለፅም እርስዎም ሲያስፈልግዎ የሚጠቀሙበትና በፖለቲካ ትችት አቀራረብ የተለመደ ነው።*

6. ***ብልፅግና ፓርቲ የሽግግር መንግሥት ጥያቄን የመቀበል እድሉ ከ10 በመቶ በላይ አይሆንም ብዬ ግምቴን ፅፌ እያለ፣ እርስዎ ግን “ፓርላማው ራሱን የሚበትን አዋጅ ሊያውጅ አይችልም” በማለት ሐሳቤ እርስ-በርሱ እንደሚጋጭ አድርገው ያቀረቡት ትችትም ስህተት ነው።*** *ፓርላማው የሽግግሩን ጥያቄ ይቀበለዋል ብዬ ባምንማ*

ኖሮ፣ 90 በመቶ ገዥው ፓርቲ የሽግግር ጥያቄውን ሊቀበለው አይችልም የሚል ግምት ባላስቀመጥኩ ነበር። ፓርላማው ያን ሊያደርግ የሚችለው የአገሪቱ የመፍትሄ አካል ለመሆን ሙሉ ፈቃደኛ ሆኖ እስከተገኘ ድረስ ብቻ ነው። ይህ የመሆን እድሉ ደግሞ እጅግ ዝቅተኛ እንደሆነ በሚገባ ገልጫለሁ። የሚጋጭ ሐሳብ የት ላይ እንደተገኘ ግልፅ አይደለም።

7. **በሰነዱ ላይ "የሽግግር ጥያቄን ዛሬ ላይ አብዛኛው ተቃዋሚ ፓርቲ ይደግፋል" አልኩ እንጅ "ሁሉም ይደግፋል" ብዬ ባልገለፅኩበት ሁኔታ፣ እርስዎ ኢዜማን እና አብንን የመንግሥት ደጋፊ መሆናቸውን እንደ ምሳሌ በመጥቀስ "የሁሉም ፓርቲዎች አቋም አንድ አይደለም" በማለት ያቀረቡት ትችትም የተዛባ መልዕክት የሚያስተላልፍ ያልተገባ ትችት ነው።** ኢዜማን እና አብንን የመሰሉት ፓርቲዎች ሽግግርን እንደማይደግፉ ሁላችንም የምናውቀው እውነታ ሆኖ እያለ  እኔ ከዚያ በተለየ ሁሉም ፓርቲ የሽግግር መንግሥት ደጋፊ እንደሆነ አድርጌ እንዳቀረብኩ አድርገው ትችት ማቅረብዎ ስህተት ነው።

8. **በጠቅላይ ሚኒስትሩ ላይ ያቀረብኩትን ትችት ተገቢ እንዳልሆነ ለማሳየት ሲሉም-  "በፓርላሜንታዊ ሲስተም ትልቁ የስልጣን አካል ጠቅላይ ሚኒስትሩ ነው" የሚለው አባባልዎ ስህተት ነው።** በኢትዮጵያ የወቅቱ ህገ መንግሥት ትልቁ የስልጣን አካል ጠቅላይ ሚኒስትሩ ሳይሆኑ ፓርላማው ነው። የሕግ ባለሞያ ሆነው እያለ እንዲህ ያለ የተሳሳተ መረጃ ማስተላለፍዎም ስህተት ነው።

በአጠቃላይ የተሻለ ይሆን የነበረው እኔ ያቀረብኳቸው ሐሳቦች ወይም ግምቶች ስህተት መሆናቸውን የእራስዎን ምክኒያታዊ ሐሳብና ግምት በማሳየት መተቸት ነበር እንጅ እንደ ፍርድ ቤት የሕግ ክርክር "መረጃ እና ማስረጃ አቅርብ" በማለት፣ የማይጋጭን ሐሳብ እንደሚጋጭ አድርጐ በማቅረብ፣ የተባለን እንዳልተባለ፣ ያልተባለን እንደተባለ አድርጐ በማቅረብ የሚቀርብ ኃላፊነት የጐደለው ትችት ወደፊትም ለምናደርገው ገንቢ ውይይት የሚጠቅመን አይመስለኝም። ለጉዳዩ ትኩረት ሰጥተው ትችት በማቅረብዎ ግን ምስጋናዬን አሁንም በድጋሜ አቀርባለሁ። ይቀጥሉበት።

ግንቦት 3 ቀን 2016ዓ.ም

***ይህንን ከዚህ በላይ የፃፍኩትን ቅሬታ ለዶ/ር ሲሳይ ከላኩላቸው በኋላ ሁለተኛው ክፍል ትችታቸው ያለፉትን ስህተቶች የማይደግም የተሻለ ትችት ይሆናል የሚል ግምት ነበረኝ። ነገር ግን ሁለተኛው ክፍል የባሰ የከፋ ሆኖ በማግሥቱ ስለቀረበ እንደገና የሚከተለውን ቅሬታዬን ጽፌ ላኩላቸው።***

ዶ/ር ሲሳይ-

በሁለተኛው ክፍል በቀረቡት ትችቶች ላይ ያየኋቸው ተጨማሪ ህጸጾች የሚከተሉት ናቸው።

9. **"ሰነዱ ተቃዋሚው ጐራ በሽግግሩ መንግሥት የሚኖረውን ድርሻ በተመለከተ- አንድ ቦታ ላይ 30%፣ ሌላ ቦታ ላይ 60% ይላል። መታረም አለበት" በሚል ያቀረቡት ትችት ስህተት ነው።** ምክኒያቱም እርስዎ  ስህተት ነው ባሉት የመጀመሪያ ክፍል (ገፅ 14፣ አንቀፅ 4) ላይ የተቀመጠው አባባል እርስዎ እንዳሉት 30% ነው የሚል ሳይሆን

“ሁለቱ የተቃዋሚ ጐራዎች እያንዳንዳቸው 30% ድርሻ ይኖራቸዋል” የሚል ነው። ይህ አባባልም የተቃዋሚው ጐራ ድርሻ በድምር 60% መሆኑን ያሳያል እንጅ 30% ነው የሚል አይደለም። በእርስዎ ደረጃ ለተማረ ሰው ይህንን ግልፅ የሆነ አገላለፅ አለመረዳት ከምን እንደመነጨ አልገባኝም። በሆነ አጋጣሚ እንዲህ አይነት ስህተት ቢገኝ እንኳ እንደ ፊደል ግድፈት ተቆጥሮ ሊታለፍ እንጂ ዋና የትችት ትኩረት መሆን አይገባውም።

10. **“አቶ ልደቱ በሽብርተኛነት ክስ ተመስርቶበታል” የሚለው አባባልዎም የተሳሳተ መረጃ ነው።** በሚዲያ “ልደቱ በሽብርተኝነት ተፈላጊ ነው” ተብሎ ከመነገሩ ውጭ እርስዎ ያወቁት እኔ የማላውቀው ምሥጢር ከሌለ በስተቀር እስካሁን በእኔ ላይ የተመሰረተ ክስ የለም። እኔም “ክስ ከተመሰረተብኝ ሕክምናዬን አቋርጬ እመለሳለሁ” አልኩ እንጅ፣ እርስዎ እንዳሉት ‘ክስ ካልተመሰረተብኝ በስተቀር ወደ አገሬ አልመለስም’ ብዬ ተናግሬ አላውቅም።

11. **ተቃዋሚው ኃይል በቀላሉ ተስማምቶ አብሮ መስራት እንደሚችል አድርጌ እንደገለፅኩ አድርገው ያቀረቡብኝ ትችትም ስህተት ነው።** እንደዚያ ብዬ ባምን ኖሮ “ተቃዋሚው ጐራ የሽግግርን ጥያቄ ለማሳካት ከ20% በላይ ዕድል ይኖረዋል ተብሎ አይገመትም” በማለት ልፅፍ አልችልም ነበር። እኔ እያልሁ ያለሁት አገሪቱ ከጥፋት እንድትተርፍ ከተፈለገ ተቃዋሚው ኃይል የግድ ተባብሮ መቆም አለበት የሚል ነው። እርስዎም እንደሚሉት  እኔም የፃፍኩት ተቃዋሚው ተባብሮ የመስራት ዕድሉ እጅግ ጠባብና ምንአልባትም ከ20% ያልበለጠ መሆኑን ነው። ለምን ባላልኩት ነገር በተቃራኒው ሊተቹኝ እንደፈለጉ አልገባኝም።

12. **ስለ ብልፅግና ፓርቲ እኔ ያለኝን አቋም ለመተቸት ሲሉ፣ “ብልፅግና ፓርቲ 13 ሚሊየን አባላት ያለው መሆኑ ከተቃዋሚዎች የተሻለ ጠንካራ የመሆኑ  ማሳያ ነው” በማለት ያቀረቡት ትችትም ምክኒያታዊ አይደለም።** ብልፅግና ፓርቲ ይህንን ያህል አባላት ሊኖረው የቻለው- አንደኛ፡ የኢህአዴግን አባላት ወርሶ በመቀጠሉ፣  ሁለተኛ፡ የተሻለ ርእዮተ-ዓለም ስላለው ሳይሆን በህገ ወጥ መንገድ የመንግሥትን መዋቅር ተጠቅሞ በአገሪቱ ዋና ስራ ቀጣሪ ሀይል በመሆኑ፣ ሦስተኛ፡ በተቃራኒው ተቃዋሚዎች ብዙ አባል ማፍራት ያልቻሉት በአገዛዙ አፈና ስለሚደርስባቸው ነው እንጅ ከብልፅግና ያነሰ የህዝብ ድጋፍ ወይም አጀንዳ ስላላቸው አይደለም። እነዚህ ሁሉ ጫናዎችና ችግሮች የተወገዱበትና እውነተኛ ዴሞክራሲ የሰፈነበት የሽግግር ሒደት ቢፈጠር ግን የሀይል ሚዛኑ ሌላ መልክ እንደሚይዝ ጥርጥር የለውም። እውነተኛ የፖለቲካ ነፃነት በአገሪቱ ቢኖር ብልፅግናን ከሌሎቹ ፓርቲዎች በተለየ በህዝብ ተመራጭ የሚያደርገው አሳማኝ ምክኒያት አሁን ላይ የለም። ‘እታምንለታለሁ’ የሚለው ርዕዮት ያለው ፓርቲም አይደለም። የቅድመ-ሽግግሩ ሒደት እስከ ስድስት ወራት ድረስ የረዘመ እንዲሆን በሰነዱ ላይ ሐሳብ የቀረበውም ሕዝቡ ከአገዛዙ አፈና ተላቆ በነፃ ፍላጐቱ የሚፈልገው ፓርቲ አባል የመሆን ዕድል እንዲኖረው ነው። የትኛው ፓርቲ በትክክል የህዝብ ድጋፍ እንዳለው በትክክል የሚረጋገጠው ያኔ ነው።

13. **በሽግግሩ ወቅት የሚቋቋሙ ኮሚሽኖች አባላት ቁጥር የተለያየ ሆኖ የቀረበውም በምክኒያት ነው እንጅ እርስዎ እንዳሉት “በአቦ-ሰጥ” አይደለም።** “አንዱ ብዙ፣ ሌላው ትንሽ ሆኖ ለምን እንደቀረበ ለእኔ ግልፅ አይደለም፣ ምክኒያቱ ተብራርቶ ቢቀርብ” ተብሎ በቅንነት ቢጠየቅ ተገቢ በሆነ ነበር። የቁጥሮቹ መልክ ስላማረኝ የመረጥኩት “የአቦ-ሰጥ” ቁጥር እንደሆነ አድርጐ ለመተቸት መሞከር ግን ቅንነት የጐደለው ነው። ምክኒያቱም የመዋቅሮቹን የኃላፊነት ዓይነት፣ ልዩ ባህሪ፣ ክብደትና ቅለት በማየት ብቻ ለምን ቁጥሩ በዚያ መልክ እንደቀረበ ለማንም ጉዳዩን በቅንነት ለማየት ለፈለገ ሰው ለመረዳት የሚከብድ አይመስለኝም። ነገር ግን በቅንነት ግልፅ ያልሆነላቸው ሰዎች ሊኖሩ ስለሚችሉም ወደፊት ጉዳዩን በዝርዝር አስረዳለሁ።

**14. "አቶ ልደቱ ስለ ወለጋ ጉዳይ ትኩረት የማይሰጠውም ከኦላ (ሸኔ) በሚያገኘው መረጃ ላይ ስለሚመሰረት ነው" በማለት ያቀረቡት ትችትም ያለቦታው የገባ እና የማይገባ አባባል ነው።** አንደኛ፡ ስለ ወለጋ በሚገባ ትኩረት እሰጣለሁ። ቢያንስ ከእርስዎ ያነሰ መረጃ አይኖረኝም። በእርግጥ በራያ ጉዳይ ከእኔ የተሻለ መረጃ እርስዎ ሊኖረዎት ይችላል። ስለ ወለጋም ሆነ ስለሌላው አካባቢ የሚኖረኝን መረጃ የምጠቀምበት ግን የሕዝቡን መጠቃት በማያባብስ ጥንቃቄና የኃላፊነት ስሜት ስለሆነ መረጃ ያጠረኝ ሊመስል ይችላል። ሁለተኛ፡ እኔ ከኦላ (ሸኔ) ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ስለሌለኝ ከእነሱ የማገኘው የተለየ መረጃ የለም። የሕግ ባለሞያ ሆነው እያለ ለምን እንደዚህ ያለ ጥንቃቄ የጐደለው ክስ ሊያቀርቡብኝ እንደፈለጉ ግን ምክንያቱ አልገባኝም።

**15. በመጨረሻም "አቶ ልደቱ ከአገር ስለወጣ የመረጃ እጥረት አለበት" በማለት ያቀረቡት ትችትም ተገቢ አልመሰለኝም።** በዚህ የመረጃ ዘመን፣ እንደ እኔ ፖለቲካን የሙሉ ጊዜ ስራው ያደረገ፣ ከሁሉም ብሄር ልሂቃን ጋር (የብልፅግና ፓርቲ አመራሮችን ጨምሮ) ከማንም በላይ የመገናኘት ዕድል ያለው የፖለቲካ ሰው ለ3 ዓመት ከአገሩ ስለዎጣ ብቻ "በቂ መረጃ" የለውም ብሎ ለመተቸት መሞከር የታሰበበት ትችት አይመስለኝም። በነገራችን ላይ በሽግግር ጥያቄ ላይ እኔ ሰነድ የፃፍኩት እርስዎ እንደሚሉት መረጃ ስለአጠረኝ እና የዳያስፖራ ፖለቲካ ተፅእኖ አድሮብኝ ሳይሆን ከአራት አመት በፊት አገሬ ላይ ሆኘ እንደነበር ቢያስታውሱ ተገቢ ይመስለኛል።

በአጠቃላይ በአንድ ትችት ውስጥ በየአንዳንዱ አረፍተ-ነገር በሚባል መጠን ይህንን ያህል የበዛ ህጸጽ ከመኖሩ እውነታ መረዳት የቻልሁት- አንድም ሰነዶቹን በሚገባ አላነበቧቸውም። ገለብ-ገለብ (Skim) አድርገው ነው ያዩአቸው። ወይንም አስቀድመው ሐሳቡን የመቃዎም አቋም ይዘው ነው በጭፍን ትችት እያቀረቡ ያሉት። ከዚህ ውጭ በአንድ አጭር ቃለ-ምልልስ ይህንን ያህል የበዛ ግድፈት አንድ ፒ. ኤች. ዲ /PHD/ ያለው እና ዩንቨርሲቲ የሚያስተምር ምሁር ሊሰራ ይችላል ብዬ ለመገመት እቸገራለሁ።

የመጀመሪያውን ክፍል ትችት አዳምጬ ቅሬታዬን ስፅፍለዎት ጉዳዩን ከቅንነት ጋር አያይዤ አላየሁትም ነበር። የሁለተኛው ክፍል ትችትዎ ያሳየኝ ግን ግምገማዎት እና ትችትዎ በኃላፊነት ስሜትና በቅንነት የቀረበ አለመሆኑን ነው። እንዲህ አይነቱ አካሔድ ለማናችንም ስለማይጠቅም ምክንያታዊ ትችት በማቅረብ ላይ ብናተኩር ተገቢ ነው እላለሁ። የወቅቱን የአገራችንን ችግር እንኳንስ በሴራና በሸፍጥ፣ በሀቅ እና በሙሉ ቅንነትም ሰርተን ለመወጣት እጅግ ከባድ ነው።

ልደቱ አያሌው

ግንቦት 4 ቀን 2016ዓ.ም

# መደምደሚያ

ይህን ቅሬታዬን ለዶ/ር ሲሳይ መንግስቴ የላኩላቸው ቢሆንም እንኳንስ ስህተታቸውን ለማረም ሊሞክሩና መልስም አልሰጡኝም። የሆነ ሆኖ ለቀጣይ ግምገማና ትችት ከዚህ የዶ/ር ሲሳይ ትችት ልንቀስም የምንችለው ቁም-ነገር አለ።

**አንደኛ፡** በአግባቡ በአላነበብነው ጽሑፍ ላይ ትችት አናቀርብ።

**ሁለተኛ፡** ስህተትን ለማረምና ተጨማሪ ግብአት ለመስጠት ብለን እንጅ አንድን ጽሑፍ እንዲሁ መተቸትን ግብ አድርገን አንተች።

**ሦስተኛ፡** የትችታችን ትኩረት በጽሑፉ ይዘት እንጅ በጸሐፊው ላይ አይሁን።

**ዐራተኛ፡** በተለይም ምሁራን ስንሆን ህብረተሰቡ የሚሰጠን አክብሮት እና ልዩ ቦታ ስላለ የምናቀርበው ትችት ጥንቃቄ እና ኃላፊነት የተሞላበት ይሁን።

**አምስተኛ፡** ተችዎች የመጀመሪያውን "መቋጫው" የሚለውን የመንደርደሪያ ሰነድ ሳያነቡ የሽግግሩን ሰነድ ባይተቹ፣

**ስድስተኛ፡** የጽሑፉን አጠቃላይ ይዘት በመረዳት እረገድ ጽሑፉ የሽግግር መንግሥት የማቋቋም ተግባር እጅግ ከባድ የሆነ እና አገሪቱ አሁን ላይ ከምትገኝበት አስቸጋሪ ሁኔታ አኳያ እውን የመሆን እድሉ የተሰጠው ግምት ከ30 በመቶ ያልበለጠ መሆኑን በውል መገንዘብ ያስፈልጋል። የሽግግር መንግሥት ማቋቋም ለህልውናችን መቀጠል ምትክ የለሽ መፍትሄ ነው የሚል እንጂ ቀላል እና የሚቻል ነው የሚል አባባል በሰነዱ ውስጥ ፈፅሞ የለም። ይህንን ካለመገንዘብ የሚሰጥ ትችት ሁሉ ተገቢ አይሆንም። በሰፊው የማየው ችግር ከዚህ ጋር የተያያዘ ነው።

**ሰባተኛ፡** አዎያዮችም ለውይይቱ አካሔድ ውጤታማነት ተብሎ እንደ አንድ አማራጭ በሰነዶቹ ግርጌ ላይ የተቀመጠውን የውይይት አካሔድ ሐሳብ አስቀድማችሁ ብታነቡት ጠቃሚ ይሆናል።

**ስምንተኛ፡** በእኔ በኩል መንግሥት እና ተቃዋሚዎች በመገዳደል ሒደት ከመቀጠልና አገርን ወደ መፍረስ አደጋ ከመውሰድ ይልቅ የሽግግር አማራጭን እንዲቀበሉ እየጠየኩ እና ይህም ጥያቄ የተቃዋሚው ጐራና የህዝብ የጋራ አጀንዳ እንዲሆን ግፊት እያደረግሁ ነው እንጅ እኔ የሽግግር መንግሥት የማቋቋም ስራ ላይ አይደለሁም። እኔ በግሌ ያን የማድረግ ፍላጐትም፣ መብትም ሆነ አቅም እንደሌለኝ መገንዘብ ተገቢ ይሆናል።

**በመጨረሻም በቀረቡት የውይይት መነሻ ሰነዶች ላይ በቀጣይ የምናደርጋቸው ግምገማዎች እና ትችቶች ምክንያታዊ፣ ኃላፊነት እና ቅንነት የተሞላባቸው እንዲሆኑ በዚህ አጋጣሚ በአክብሮት ጥሪዬን አቀርባለሁ።**

ልደቱ አያሌው

ግንቦት 7 ቀን 2016 ዓ.ም